በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቀን ሕዳር 03 2012
Date
ቁጥር 4/0313/12
Ref.No.

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ
በያሉበት

**ጉዳዩ፡- የቀረጥና ታክስ ነፃ አፈ.ቃቀድን ይመለከታል፡፡**

4/0255/12 ጥቅምት 15 ቀን 2012 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በጉምሩክ አዋጅ 859/2006 ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት እንዲፈቅዱ በህግ ለሌሎች የመንግስት አካላት ተሰጥቶ የነበረው ሥልጣን ለገንዘብ ሚኒስቴር መተላለፉ የተደነገገ ስለሆነ ከዚህ ድንጋጌ ውጭ በማናቸውም የመንግስት አካላት ተፈቅደው ለሚቀርቡ የቀረጥ ነፃ መብቶች አገልግሎት የማንሰጥ መሆኑ ታውቆ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጁ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ተፈቅደው ለሚቀርቡ ጉዳዮች ብቻ አገልግሎት እንዲሰጥ ማሳወቃችን ይታወሳል፡፡

ነገር ግን ገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ቀ/ነ/ተ/14/92 ቀን 21/02/2012 በተጻፈ ደብዳቤ የፌደራል አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀጽ 6 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የፌደራል አስፈጻሚ አካላት በህግ ከተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባራት በከፊል ለሌላ የፌደራል ወይም የክልል አካላት በውክልና ሊሰጡ እንደሚችሉ በተደነገገው መሠረት የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነጻ የሚያስገቡበት ሁኔታ ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 41/2007 (እንደተሻሻለው) በአንቀጽ 8 ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጡትን ተግባራትና ኃላፊነቶች ማከናወኑን እንዲቀጥል በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወከለ መሆኑን ገልጸልናል፡፡

በመሆኑም የገንዘብ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነጻ የሚያስገቡበት ሁኔታ ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 41/2007 (እንደተሻሻለው) በአንቀጽ 8 መሰረት የተሰጡትን ተግባራትና ኃላፊነቶች ማከናወኑን እንዲቀጥል የተወከለ በመሆኑ በዚሁ አግባብ የጉምሩክ አገልግሎት እንዲሰጥ እያሳሰብኩ ለአፈጻጸም ይረዳችሁ ዘንድ የገንዘብ ሚኒስቴር ውሳኔ ደብደቤ 01 ገጽ አባሪ በማድረግ የተላከላችሁ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

ለዘመናዊና ፍትሀዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

☏ +251 116 62 98 00
📠 +251 116 62 98 19
✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

**ለስቸኳይ**

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ**
**ገንዘብ ሚኒስቴር**
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር Ref.No. ቁ/ገ.1ታ/14/92
ቀን Date 21/9/2012

ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
ለገቢዎች ሚኒስቴር
ለጉምሩክ ኮሚሽን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- <u>የእንቅስቃሴ ችግር ላለባቸው አካል ጉዳተኞች የግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ የቀረጥ ነፃ መብት መፍቀድን ይመለከታል፡፡</u>

በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 41 ንዑስ አንቀፅ 5 መንግስት የሀገራችን ኢኮኖሚ አቅም በፈቀደ መጠን አካል ጉዳተኞችን ለመርዳት የሚያስችል ድጋፍ እንደሚያደርግ ተደንግጓል፡፡ ይህንን መሠረት በማድረግ በአካል ጉዳታቸው ምክንያት ከቦታ ወደ ቦታ የመንቀሳቀስ ችግር ያለባቸውን አካል ጉዳተኛ ዜጎች ለማገዝ እንዲቻል ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ እንዲገዙ የሚፈቅድ መመሪያ በመ/ቤታችን ወጥቶ እየተሰራበት ይገኛል፡፡

መመሪያው የእንቅስቃሴ ድጋፍ የሚሹ አካል ጉዳተኞች የተሽከርካሪ ቀረጥ ነፃ መብት ተጠቃሚ ለመሆን ማሟላት የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች የሚወስን ሲሆን እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልተው የግል ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ ጥያቄ የሚያቀርቡ አካል ጉዳተኞች በመመሪያው የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላታቸውን በማረጋገጥ የቀረጥ ነፃ መብቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለጉምሩክ ኮሚሽን የድጋፍ ደብዳቤ የመፃፍ ሃላፊነት ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተሰጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ ማንኛውም የቀረጥ ነፃ መብት በገንዘብ ሚኒስቴር ብቻ እንዲፈቀድ የሚደነግገው የጉምሩክ አዋጅ ማሻሻያ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቆ በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ መዋሉን ተከትሎ አካል ጉዳተኞች የቀረጥ ነፃ መብቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥያቄያቸውን ለገንዘብ ሚኒስቴር ማቅረብ እንደሚገባቸው በጉምሩክ ኮሚሽን የተገለፀላቸው መሆኑን በመጥቀስ የመብቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለመ/ቤታችን ጥያቄ በማቅረብ ላይ ናቸው፡፡

መ/ቤታችን አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ የሚወስን መመሪያ ያወጣ በመሆኑ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በመመሪያው የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልተው የሚገኙ አካል ጉዳተኞች የመመሪያው ተጠቃሚ መሆን እንደሚችሉ በማረጋገጥ መመሪያውን ማስፈፀም እንዲቀጥል ማድረጉ ለአሰራር አመቺ እንደሆነ ታምኖበታል፡፡

ስለዚህ የፌዴራል አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 6 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የፌዴራል አስፈፃሚ አካላት በሕግ ከተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባራት በከፊል ለሌላ የፌዴራል ወይም የክልል አካላት በውክልና ሊሰጡ እንደሚችሉ በተደነገገው መሠረት የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 41/2007 (እንደተሻሻለው) በአንቀፅ 8 ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጡትን ተግባራትና ኃላፊነቶች ማከናወኑን እንዲቀጥል በመ/ቤታችን የተወከለ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሚኒስትር ዴኤታ

Lerrer/Tw/TA

ስልክ
Tel 251- 11- 155 24 00.22 66.98 P.O.Box 1905,1037 Fax 251-11-156 01 24.55 14 96 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
251- 11- 155 00 81.83 86 89 እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ 251-11-155 11 38 Addis Ababa-Ethiopia

- ለአማራ ብ/ክ/መ/ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ

  <u>ባህርዳር</u>

- ለትግራይ ክልል ኢንቨስትመንት ቢሮ

  <u>መቐሌ</u>

- ለኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን

  <u>ኦሮሚያ</u>

- ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ኢንቨስትመንት ኮሚሽን

  <u>ሐዋሳ</u>

- ለአፋር ክልል ኢንቨስትመንት ቢሮ

  <u>ሰመራ</u>

- ለቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል መንግስት አካባቢ መሬት አስተዳደር እና ኢንቨስትመንት ቢሮ

  <u>ቤንሻንጉል</u>

- ለሱማሌ ክልል ኢንቨስትመንት ቢሮ

  <u>ጅግጅጋ</u>

- ለድሬዳዋ ከንቲባ ንግድና ኢንቨስትመንት ቢሮ

  <u>ድሬዳዋ</u>

- ለጋምቤላ ክልል ኢንቨስትመንት ቢሮ

  <u>ጋምቤላ</u>

- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊሲ ኮሚሽን
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የህብረት ስራ ኤጀንሲ
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌዴራል አነስተኛ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ኤጀንሲ

  <u>አዲስ አበባ</u>

- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  አዲስ አበባ
- ለሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ሞጆ
- ለአዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  አዳማ
- ለድሬዳዋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ድሬዳዋ
- ለጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ጅግጅጋ
- ለሀዋሳ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ሀዋሳ
- ለጅማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ጅማ
- ለሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ሞያሌ
- ለአዋሽ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  አዋሽ
- ለጋላፊ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ጋላፊ
- ለኮምቦልቻ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ኮምቦልቻ
- ለመቀሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  መቀሌ
- ለባህርዳር ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ባህርዳር
- ለጅቡቲ ጉምሩክ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
  ጅቡቲ

ግልባጭ/

- ለሰላም ሚኒስቴር
- ለአገር መከላከያ ሚኒስቴር
- ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
- ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ
- ለግብርና ሚኒስቴር
- ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
- ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
- ለትራንስፖርት ሚኒስቴር
- ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
- ለውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር
- ለማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
- ለትምህርት ሚኒስቴር
- ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
- ለጤና ሚኒስቴር
- ለሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር
- ለሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
- ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
- ለገቢዎች ሚኒስቴር
- ለገንዘብ ሚኒስቴር

  አዲስ አበባ

- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ

  ጉምሩክ ኮሚሽን

- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን

  አዲስ አበባ

- አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት ኮሚሽን

  አዲስ አበባ